ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

ፀረ-ሙስና ቅጽ 2 ቁጥር 29 ጥቅምት 30/2018 ዓ.ም

ስሙስና ወንጀል ጥቆማ

ሞባይል መተግበሪያ፦ **NCRS**

ስልክ፦ 0953222255
0953222299

ይጠቀሙ!

ስተጨማሪ መረጃ :-
www.feacc.gov.et
ይጎበኙ

## በውስጥ ገጾች

ኮሚሽኑ ህግና መመሪያን የጣሰ የጨረታ ግዢ ሂደት እንዲቋረጥ አደረገ
ገጽ 2

ኤጀንሲው የሥነምግባር ጥሰት በፈፀሙ 18 ሰራተኞች እርምጃ መውሰዱን ገለፀ
ገጽ 3

በፎቶ ቤት ውስጥ ሀሰተኛ ሰነድ ሲያዘጋጁ የነበሩ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ዋሉ
ገጽ 4

## ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ 8 ሺህ 613 አመራሮች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃ ተወስዷል፡፡

አቶ አደም ፋራህ






ኃላፊነቱን በሚገባ በማይወጣ እና ሕዝቡን በታማኝነት በማያገለግል አመራር ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ፕሬዚዳንት እና የዋና ጽ/ቤት ኃላፊ ክቡር አቶ አደም ፋራህ ገለፁ፡፡ ኃላፊው በማብራሪያቸውም ባለፉት ሶስት ወራት የፓርቲውን ተቋማዊ አቅም የሚያጠናክሩ ሥራዎች መከናወናቸውን አብራርተው የአመራርና የአባላት ግምገማ እና ምዘና በማካሄድ እውቅና እና ምስጋና መሰጠቱን ገልፀዋል፡፡ በአንፃሩ ኃላፊነታቸውን ባልተወጡ 8 ሺህ 613 አመራሮች ላይ የዲሲፕሊን እርምጃዎች መወሰዱን አመላክተው በቀጣይም ኃላፊነት በሚገባ በማይወጡ፣ ሕዝቡን በቅንነትና በታማኝነት በማያገለግሉ፣ በሙስና እና ብልሹ አሰራር ውስጥ በሚዘፈቁ አመራሮች ላይ የሚወሰደው እርምጃ ተጠናክሮ እንደሚቀጥልም አረጋግጠዋል፡፡

## ኮሚሽኑ የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ስርዓት (Ethiopian Asset Registration System- EARS) ላይ ተግባር ተኮር ስልጠና ሰጠ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ለዘርፍ ተቋማት የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች የዲጂታል ሀብት ምዝገባ ሥርዓት (EARS) አመዘጋገብ ላይ ተግባር ስልጠና ሰጥቷል፡፡

ስልጠናው በዋናነት በበጀት አመቱ የዘርፍ ተቋማት ሥራ አስፈፃሚዎችና ሠራተኞች ሀብታቸውን በአግባቡ እንዲያስመዘግቡ እና እንዲያሳትፉ ለማድረግ የተዘጋጀ ነው፡፡



በስልጠናው ከ70 በላይ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ሆልዲንግ እና ተጠሪ ተቋማት የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና አስፈፃሚዎች፣ የመረጃ እና የአይሲቲ ባለሙያዎች ተሳትፈዋል፡፡

ስልጠናው ቀደም ሲል በተለያየ ጊዜ ለዘርፍ ተቋማት የሥነምግባር እና ፀረ-ሙስና ሥራ አስፈፃሚዎችና ባለሙያዎች መሰጠቱ ይታወሳል፡፡



# ኮሚሽኑ ህግና መመሪያን የጣሰ የጨረታ ግዢ ሂደት እንዲቋረጥ አደረገ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የኢፌዲሪ ሰላም ሚኒስቴር 5 ሚሊዮን ብር በላይ በሆነ ገንዘብ ባወጣው የበጎ ፈቃድ ሠልጣኞች ቲሸርት ግዥ ግልፅ ጨረታ ሂደት ላይ የአስቸኳይ ሙስና መከላከል የአሠራር ሥርዓት ግልፅነት ጥናት አካሂዷል።

ጥናቱም የግዥ ሂደቱ ግልፅና ዝርዝር መለያ መስፈርት ያልተቀመጠለት፣ የገበያ ጥናት ያልተካሄደበት እና የተጫራቾችን ተሳትፎ በሚገድብ ሁኔታ መከናወኑን አመላክቷል።

በጥናቱ ግኝት ላይ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እና የኮሚሽኑ ከፍተኛ አመራሮች እና የሥራ ኃላፊዎች በተገኙበት የውይይት መድረክ ተካሂዷል።

በውይይቱ መጨረሻም በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እየተካሄደ ያለው የበጎ ፈቃድ ሠልጣኞች ቲሸርት ግዥ ጨረታ ሂደት እንዲቋረጥ እና ግዥው አሠራርን ጠብቆ እንዲካሄድ ውሳኔ የተሰጠ ሲሆን የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ አመራሮችም በቀጣይ ተመሣሣይ ችግሮች እንዳይከሰቱ ማሻሻያዎችን እንደሚያደርጉ መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡







# ታዳጊዋ የሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርን መቆጣጠሪያ ሲስተም እንዳበለፀገች ተገለጸ

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለ4ተኛ ጊዜ በ2017 ዓ.ም ባዘጋጀው የሳይበር ታለንት ሰመር ካምፕ ፕሮግራም ከተሳተፉና ከተመረቁ ባለልዩ ተሰጥኦ ታዳጊ ወጣቶች መካከል አንዷ ናኦሚ ጎዝጉዜ ናት፡፡ ናኦሚ በሰመር ካምፕ ቆይታዋ ሕገ ወጥ የገንዘብ ዝውውርን ለመቆጣጠር የሚያስችል ሲስተም (Anti-Money Laundry - AML) እንዳበለጸገች ተገልጧል፡፡

ይህ ፕሮጀክት በህገወጥ መንገድ የተገኘን ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብን (Money laundry) ለመከላከል ታስቦ የተሰራ ነው፡፡ ይህ ስርዓት አጠራጣሪ፣ ሕገ-ወጥ ወይም ያልተለመዱ የፋይናንስ እንቅስቃሴዎችን ወይም ግብይቶችን ይከታተላል፤ ይለያል፣ ከዚህም ባሻገር ለህግ አስከባሪዎች የወንጀል ምርመራን በማቅለል ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር - INSA ከአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ጋር በመተባበር ለ4ተኛ ጊዜ ባዘጋጀው የሳይበር ታለንት ሰመር ካምፕ ፕሮግራም፣ 629 ባለልዩ ተሰጥኦ ታዳጊ ወጣቶች የተመረቁ ሲሆን፤ ተመራቂዎቹ በግልና በቡድን በመሆን 31 ችግር ፈቺ የሆኑ ፕሮጀክቶችን መስራታቸውን/ማከናወናቸውን የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አስተዳደር (ኢመደአ) በፌስቡክ ገጹ አስፍሯል፡፡



# ኤጀንሲው የሥነምግባር ጥሰት በፈፀሙ 18 ሰራተኞች እርምጃ መውሰዱን ገለፀ

የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ የሥነምግባር ጥሰት ሲፈጽሙ በተገኙ አመራሮችና ተገልጋዮች ላይ እርምጃ መውሰዱን አስታውቋል፡፡

ባለፉት 3 ወራት በስነምግባር ጥሰት ተግባር ላይ ሲሳተፉ በተገኙ 18 አመራሮች እና ተገልጋዮች ላይ እርምጃ እንደተወሰደ የኤጀንሲው ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ጥጋቡ ሹመይ ተናግረዋል፡፡

አክለውም በተለይ የስነምግባር ጥሰት በፈፀሙ አመራሮች ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ ከመውሰድም ባሻገር ጉዳዩን ፍርድ ቤት እያቀረበ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ባለሙያዎችን ለስነምግባር ጥሰት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ አሰራሮችን በመለየት ለማሻሻል ኤጀንሲው በትኩረት እየሰራ መሆኑን የገለጹት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፤ ዲጂታል አሰራር ስርአት እየተዘረጋ መሆኑንና በቅርቡ ስራ ላይ እንደሚውል አስታውቀዋል፡፡

CRRSA
የሲቪል ምዝገባ እና የነዋሪነት አገልግሎት ኤጀንሲ

# ክልሉ የሙስና መከላከል ሥራዎችን በትኩረት እየሰራ መሆኑን ገለጸ

የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ህዝቦች ክልል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የ2018 በጀት የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የሙስና መከላከል ሥራዎች አፈፃፀም ሪፖርት በዝርዝር መገምገሙን የኮሚሽኑ ኮሚሽነር አቶ ሙሉሰዉ ዘዉዴ ገልፀዋል፡፡

ኮሚሽኑ በሩብ ዓመቱ 103 የተለያዩ የሙስና ጥቆማዎችን የተቀበለ ሲሆን ከዚህ ውስጥ 45 የሙስና ጥቆማዎችን በአስቸኳይ ሙስና መከላከል በሂደት ላይ የሚገኙ የሙስና ወንጀሎች ወደ ድርጊትከመለወጣቸው በፊት እንዲቋረጥ መደረጉን ጠቅሷል።

በሌላ በኩል 16 የሙስና ጥቆማዎች በአስተዳደራዊ እርምጃ መፈታቱን፣ በ19ኙ ላይ የምክር አገልግሎት መሰጠቱን፣ ስምንት ጥቆማዎች ለፍትህ ቢሮ መተላለፉን እንዲሁም በ15ቱ ላይ የማጣራት ሥራ እየተካሄደ መሆኑ ተገልጿል።

በከተማና ገጠር አከባቢዎች ሀሰተኛ የመሬት ይዞታ ማረጋገጫ ጋር ተያይዞ የሚደረሱ ሙስና እና ብልሹ አሠራሮችን ለመከላከል ዘርፈ ብዙ ተግባራት የተከናወነ መሆኑ ተመላክቷል።

ከሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ጋር በተያያዘ በሩብ ዓመቱ 697 አዲስ ሠራተኞች የሀብት ምዝገባ ያስመዘገቡ ሲሆን ሀብታቸውን ለማስመዝገብ ፍቃደኛ ያልሆኑ 26 የመንግሥት ሠራተኞች እያንዳንዳቸው ከአንድ ሺህ ብር ቅጣት ጋር ሀብታቸውን እንዲያስመዘግቡ መደረጉ ተገልጿል።

በመጨረሻም ኮሚሽነሩ ዜጎች ማንኛውንም አገልግሎቶች ከተቋማት ለማግኘት በሚያደርጉት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚያጋጥማቸውን ሙስና እና ብልሹ አሠራር በቁርጠኝነት በማጋለጥ ለፀረ-ሙስና ትግል የበኩላቸዉን እንዲወጡ ጥሪ አቅርበዋል።



# የፌዴራል ማረሚያ ቤት ኮሚሽን የሥነምግባር ጥሰቶችን ለመቅረፍ በቁጭት ሊሰራ ይገባል - ክቡር ኮሚሽነር ጄኔራል ደመላሽ ገብረሚካኤል

ክቡር ኮሚሽነር ጄኔራል ደመላሽ ገብረሚካኤል በማረሚያ ቤቶች በነበራቸው ጉብኝት በሥራ ላይ ከሚገኙ የፌዴራል ፖሊስ አባላት ጋር በመገናኘት ለቀጣይ ሥራ የሚያነሳሳ መልዕክት በማስተላለፍ የፖሊስ አባላቱ በፖሊሳዊ ሥነ ምግባር ታግዘው በየተሰማሩበት የሥራ መስክ የሚያስመሰግን ሥራ እንዲሠሩ መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል፡፡ ሌላው የማረሚያ ቤቱ ኮሚሽን የፋይናንስና ሰው ሀብት ልማት ዘርፍ ም/ኮሚሽነር ጄኔራል ደስታ አስመላሽ በተቋሙ ውስጥ የሚስተዋሉ የሥነ ምግባር ጥሰቶችን ለመቅረፍ መንግሥት በአስቀመጠው አቅጣጫ መሠረት ከ1,100 በላይ አመራሮችና አባላት ግምገማዊ ስልጠና ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።





## ፕሮጀክቶች ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ እንዲሰሩ የፀረሙስና ኮሚሽን ሚናውን በአግባቡ እንደሚወጣ ገለፀ።

በአለም ባንክ ድጋፍ በክልሉ የሚከናወኑ የገጠር ትስስርና ተደራሽነት ለምግብ ዋስትና የመንገድ ግንባታ ፕሮግራም/RCFSP/ ስራ ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ ሁኔታ እየተከናወነ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ በስነምግባርና ፀረሙስና ኮሚሽን የተደረገውን የመስክ ምልከታ ሪፖርት ኮሚሽኑ ገምግሟል ።

በክልሉ ዘጠኝ ወረዳዎች እና በ56 ቀበሌያት 630,306, 345.03 ብር ( ስድስት መቶ ሠላሳ ሚልዮን ሦስት መቶ ስድስት ሺ ሦስት መቶ አርባ አምስት ብር ከዜሮ ሦስት ሳንቲም) የገጠር ለገጠር ትስስር ለመፍጠር ያለመ የመንገድ ግንባታ ፕሮጀክት እየተከናወነ ስለመሆኑ ታውቋል።

በፕሮጀክቶቹ ግንባታ ላይ ጠንካራና ደካማ ጎኖች የተለዩ ሲሆን ከሚመለከታቸው ባለድርሻ ተቋማት ጋር በቀጣይ ምክክር እንደሚደረግበት ኮሚሽኑአሳውቋል።

በክልሉ የሚከናወኑ ሁሉም ፕሮጀክቶች በታቀደላቸው ጊዜና ጥራት ተጠናቀው ለህብረተሰቡ አገልግሎት እንዲውሉ ከሙስናና ብልሹ አሰራር በፀዳ መልኩ እንዲተገበር ኮሚሽኑ ሚናውን በአግባቡ እንደሚወጣ ገልጿል ።

# ባለስልጣኑ የሙያ ስነምግባር ግንባታ ለአገልግሎት አሰጣጥ በሚል ርዕስ ስልጠና ሰጠ

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን፥ የሙያ ስነምግባር ግንባታ ለአገልግሎት አሰጣጥ፥ በሚል መሪ ቃል ለባለስልጣኑ አመራሮችና ሰራተኞች ስልጠና ሰጥቷል፡፡

በስልጠናው የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት በባለስልጣኑ የአስተዳደርና ፋይናንስ ዘርፍ ምክትል ስራ አስኪያጅ አቶ ፍሬው ሰማ የሙያ ስነምግባር በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የመልካም አስተዳደር ችግሮችን በመለየት የተገልጋይን እርካታ የማረጋገጥ ሥራ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

አያይዘውም በተቋሙና በተገልጋይ መካከል ያለውን ትስስርና እምነት ማጠናከር የሚቻለው ተደራሽ፣ አካታች እና ፍትሃዊ አገልግሎትን በማረጋገጥ እንደሆነ ለአመራሮችና ሰራተኞች





መልዕክት አስተላልፈዋል።

ስልጠናውን የሰጡት የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፍቃድ ቁጥጥር ባለስልጣን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ወ/ሮ ፋንቱ ረጋሳ ስልጠናው መልካም ስነምግባር እንዲጎለብት፣ ከሙስናና ብልሹ አሰራር የፀዳ አገልግሎት





እንዲሰጥ ሰራተኞችና አመራሮች ቁልፍ ሚና እንዳላቸው ተናግረዋል። ስልጠናው ሙያዊ ስነምግባርና ጥራት ያለው የህዝብ አገልግሎት ለመስጠት ያለውን ሚና ለማጠናከር ያለመ መሆኑንም ተናግረዋል።

# በፎቶ ቤት ውስጥ ሀሰተኛ ሰነድ ሲያዘጋጁ የነበሩ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ስር ዋሉ

የአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ ፖሊስ መምሪያ ከህብረተሰቡ በደረሰው ጥቆማ መነሻነት ባደረገው ክትትል አበበ አሰፋ እና ፍቃዱ ሳሙኤል የተባሉ ተጠርጣሪዎች ሀሰተኛ ሰነድ ሲያዘጋጁ በቁጥጥር ስር ማዋሉን ገልጿል።

ተጠርጣሪዎቹ በክፍለ ከተማው ወረዳ 6 ልዩ ቦታው ጎጀም በረንዳ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ በህጋዊ ንግድ ሽፋን የተለያዩ ህገ-ወጥ ተግባር የሚፈፅሙ ስለመሆናቸው በምርመራው ሂደት ማወቅ መቻሉ ተዘግቧል።





# ዩኒቨርሲቲዎች የ2018 የሥነምግባር እጩ አምባሳደር ተማሪዎች ልየታ ውድድር ጀመሩ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 1236/2013 አንቀፅ 6 መሠረት ከተቋቋመበት ዓላማዎች አንዱ የትውልድ ሥነምግባር እና የሞራል እሴቶችን በብቃት መገንባት ነው፡፡ በዚሁ መሰረት በመንግስትና ግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የትውልድ ስነምግባር ግንባታን ለመስራት የተማሪዎች የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ክበብ የአደረጃጀትና የአሰራር ስታንዳርድ ወጥቶ እየተሰራበት ይገኛል፡፡ ኮሚሽኑ በ2018 በጀት ዓመት ከያዛቸው የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል እቅዶች መካከል አንዱ በመንግስትና በግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና የፌደራል የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች የሥነምግባርና የፀረሙስና ክበባት ላይ አገር ዓቀፍ የእጩ የሥነምግባር አምባሳደር ምልመላ መስፈረት በማዘጋጀት መመልመል፣በአገር ዓቀፍ ደረጃ ማወዳደርና ዕውቅና ቀጣይ ተልዕኮ መስጠት ነው፡ ፡ በተቋማት የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ክበባት ውስጥ አባል ሆነው መስፈርቱን የሚያሟሉ ተማሪዎችን በመለየት በትውልድ የሥነምግባር ግንባታና ሙስና መከላከል ዙሪያ በተዘጋጁ ጥያቄዎችና መልስ እንዲሁም የሀሳብ ክርክሮችን በማካሄድ የውድድሩ የአሸናፊዎች አሸናፊ የሆኑ ተወዳዳሪዎች እውቅናና ሽልማት ለመስጠት፣ የተማሪዎች የስነምግባር አምባሳደር ለመምረጥና በትውልድ የሥነምግባር ግንባታ ዙሪያ ንቅናቄ እንዲፈጠር ለማድረግ የሥነምግባር እጩ አምባሳደር ተማሪዎች ልየታ ውድድር እየተካሄደ ይገኛል፡፡ ውድድሩ በዋናነት የስነ-ምግባርንና የሙስናን ጉዳዮችን መሰረት ያደረጉ ጥያቄዎች በስነ-ዜጋ ት/ት ክፍል መምህራን የተዘጋጁ ሲሆን ጥያቄዎቹም የተማሪዎቹን ግንዛቤ ከመፈተሽም ባሻገር በሀገር ዓቀፍ ደረጃ ለሚኖራቸው የስነ-ምግባር አምባሳደር ውድድር በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚያዘጋጅ ተገልጽዋል። የ2018 የሥነምግባር እጩ አምባሳደር ተማሪዎች ልየታ ውድድር ከጀመሩ ዩንቨርስቲዎች መካከል ጋምቤላ፣ ሰላሌ፣ አዲግራት፣ ቦንጋ፣ አዳማ ሣይንስና ቴክኖሎጂ፣ አምቦ፣ ደብረ ማርቆስ እና ወለጋ ዩኒቨርሲቲ ናቸው፡ ፡

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# ፀረ-ሙስና

## በፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን በየ15 ቀን የሚዘጋጅ ጋዜጣ

ፖ.ሳ.ቁ 34799
ኢ-ሜይል FeaccEthiopia2013@et
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ፌስቡክ www.facebook.com/feaccOfficial
ቴሌግራም t.me/feacc
ትዊተር www.twitter.com/EthiopiaFeacc
ዩቲዩብ Federal Ethics & Anti-Corruption Commission

**ለሀብት ማሳወቅና ምዝገባ ስራዎች**
**EARS**

## ለፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን የሙስና ወንጀል ጥቆማ መስጫ አድራሻዎች

ሞባይል 0953222255
0953222299
ፖ.ሳ.ቁ 34799
ድረ-ገጽ www.feacc.gov.et
ቴሌግራም t.me/CorruptionPointing
ዋትስአፕ wa.me/qr/5IGXTSIYUMPBF1

**NCRS**

# ርዕሰ -አንቀፅ

## ተቋማት ሥነምግባራዊ አሰራርን በማጎልበት ሙስናን ሊከላከሉ ይገባል!

ሙስና ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እድገትን በመግታት በሀገር ላይ ከፍተኛ ቀውስን የሚያስከትል ወንጀል ነው፡፡ ይህንን ወንጀል በቁርጠኝነት መከላከል ያስፈልጋል፡፡ በዚህም በተቋማት ታማኝነትን፣ የአሠራር ግልጽነትን፣ የህግ ተጠያቂነትን እና ፍትሃዊ የአገልግሎት አሠጣጥ ባህልን በመገንባት ሥነምግባራዊ አሰራርን ማስፈን አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው።

ተቋማት የሥነምግባር ግንባታ እና ሙስና መከላከልን ሥራን የዋና ዕቅዳቸው አካል በማድረግ ሁሉም ሥራ ክፍሎች ዕቅዱን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ቁርጠኛ አመራር ሊሰጥ ይገባል፡፡ ሌላው የሚሰጡ ውሳኔዎች ከጥቅም ግጭት ነፃ ሆነው መከናወናቸውን በሥነምግባራዊ አመራርነት መከታተልና መገምገም የቅድሚ ቅድሚያ የሚሰጠው ወሳኝ ተግባር ነው፡፡

ለዚህም ከተቋማት የሥራ ባህሪ ጋር የሚጣጣም ሥነምግባራዊ መመሪያን ማውጣት እና ማስፈጸም፣ በተደጋገሚ የሥነምግባር ግንባታ ስልጠና መስጠት፣ የግልጽነት እና ተጠያቂነት አሠራርን መዘርጋት እና ማስፈን፣ የማበረታቻ ሥርዓትን ተግባራዊ ማድረግ እና ወዘተ ሙስና እና ብልሹ አሠራርን ዕለት ተዕለት መታገል ይገባል፡፡

# ከሙስና ምርመራ ዘገባ ማህደር

## በመንግስት ላይ 52 ሚሊየን ብር ኪሳራ አድርሰዋል የተባሉ ግለሰቦች በከባድ የሙስና ወንጀል ተከሰሱ

የቀድሞ የፕራይቬታይዜሽን እና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ይዞታና አስተዳደር ኤጀንሲ ዋና ዳይሬክተርን ጨምሮ በመንግስት ላይ 52 ሚሊየን ብር ኪሳራ አድርሰዋል የተባሉ ሦስት ግለሰቦች በከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ተመስርቶባቸዋል፡፡

ተከሳሾቹ በመንግስት ይዞታ ስር ሲተዳደር የነበረው አደይ አበባ ድርና ማግ ፋብሪካ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ልብስ ስፌትና ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ እንዲቀየር አድርገዋል በሚል ነው ክስ የተመሰረተባቸው፡፡

1ኛ ተከሳሽ የኤጀንሲው ዋና ዳይሬክተር የነበሩት በየነ ገ/መስቀል ማዳ፣ 2ኛ ተከሳሽ የኤጀንሲው የድህረ ፕራይቬታይዜሽን ንግድና አገልግሎት ዘርፍ ዳይሬክተር ታዬ አድማሱ አዘነ እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ የቢኤም ኢትዮጵያ ልብስ ስፌትና ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ ስራ አስኪያጅ የነበሩት ዋን ሚዩንግ ራዩ ናቸው፡፡

1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች የማይገባ ጥቅም ለማግኘት በማሰብ በግል ሥራ ዘርፍ ከተሰማራው 3ኛ ተከሳሽ ጋር በጥቅም በመመሳጠር ፋብሪካውን ተገቢ ባልሆነ መንገድ ወደ ኢትዮጵያ ልብስ ስፌትና ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ እንዲቀየር ማድረጋቸው በክሱ ላይ ተመልክቷል፡፡

አደይ አበባ ድርና ማግ ብሎክ-2 ፋብሪካ በጋራ ኢንቨስትመንት ስምምነት ከግል አልሚ ባለሀብቶች ጋር አክሲዮን ማህበር ሆኖ እንዲመሰረት በቦርድ በተወሰነው መሰረት በቀን 08/02/2003 ዓ.ም 1ኛ እና 3ኛ ተከሳሽ የጋራ ኢንቨስትመንት ስምምነት ውል መፈራረማቸውን የክስ መዝገቡ አስታውሷል፡፡

3ኛ ተከሳሽ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የብር ምንዛሪ ተመን የሚሰላ 10 ሚሊየን 993ሺ.ህ ዶላር በአክሲዮን ድርሻን መመዝገብ እንዳለበትና ከዚህ ውስጥ 3 ነጥብ 2 ሚሊየን ዶላር በወቅቱ የምንዛሪ ስሌት 52 ሚሊየን 576 ሺ.ህ ብር መክፈል እንዳለባቸው በስምምነቱ ተካቷል፡፡

ይህ ካልተፈጸመ አክሲዮን ማህበሩ እንደማይቋቋምና ውሉም እንዳልተፈጸመ እንደሚቆጠር ተዋውለው የነበረ ቢሆንም ስምምነቱን በሚጣረስ መልኩ 3ኛ ተከሳሽና እሱ የመረጣቸው ሌሎች ሦስት ባለድርሻዎች ያልተገባ ጥቅም እንዲያገኙ በማሰብ 1 ሚሊየን 643 ሺ.ህ ብር ብቻ በመክፈል ፋብሪካው ቢኤም ኢትዮጲያ ልብስ ስፌትና ጨርቃ ጨርቅ አ.ማ ሆኖ እንዲመሰረት ማድረጋቸው በክስ ዝርዝሩ ላይ ሰፍሯል ፡፡

በዚህም ዐቃቤ ህግ 1ኛ እና 2ኛ ተከሳሾች መንግስት ከተከፈለ አክሲዮን ድርሻ መዋጮ ማግኘት ያለበትንና ሊጠበቁት የሚገባ 52 ሚሊየን 576 ሺ.ህ ብር ጥቅም በማሳጣት እንዲሁም 3ኛ ተከሳሽ የማይገባ ጥቅም እንዲያገኝ አድርገዋል በማለት በ1996 ዓ.ም የወጣውን የኢፌዴሪ የወንጀል ህግ አንቀጽ 32 (1) (ሀ)፣ 33 እና 411 (1) (ሀ) (ሐ) (2) ላይ የተመለከተውን በመተላለፍ በዋና ወንጀል አድራጊነት ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ መስርቶባቸዋል፡፡

በተጨማሪም 3ኛ ተከሳሽ በልዩ ወንጀል አድራጊነት ተካፋይ በመሆን በፈጸሙት የመንግስት ሥራን በማይመች አኳኋን መምራት ከባድ የሙስና ወንጀል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡

በሌላ ዜና ሀሰተኛ የውጭ ሀገር ገንዘብ ሊመነዝር የነበረ ግለሰብ በእስራት ተቀጣ

ቷል በምስራቅ ባሌ ዞን ጊኒር ከተማ ውስጥ ሀሠተኛ ባለ አምስት መቶ የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶች ድርሃም ብዛቱ ሁለት ሺሕ አምስት መቶ የብር ኖቶችን ባንክ ቤት ሔዶ ወደ ኢትዮድያ የብር ኖት ለመቀየር የሞከረው ግለሠብ በእስራት መቀጣቱ የዞን ፖሊስ ዋና መምሪያ ገልጧል፡፡

ተከሳሽ አብድል ሽኩር አብደላ የተባለ የጊኒር ከተማ ነዋሪ መስከረም 6 ቀን 2018 ዓም ከቀኑ ሠባት ሠዓት ተኩል ላይ የባንክ ቤት ሰራተኞች በደንበኞች መስተግዶ በተጨናነቁበት ሠዓት ሀሠተኛ ብሩን ለመቀየር ያደረገው ጥረት ሳይሣካ በቁጥጥር ስር ውሏል፡፡

ሀሠተኛ የተባበሩት አረብ ኢሚሬቶች የብር ኖቱ አንድ መቶ ሐያ አራት ሺሕ ሑለት መቶ ሠላሣ አምስት ብር እንደሆነ ከባንክ የተገኘው መረጃ ያመለከተ ሲሆን በቁጥጥር ስር የዋለው ሁለት ሺሕ ድርሃም በሙሉ ሐሠተኛ መሆኑንም በማሽን በታገዘ ምርመራ ተረጋግጧል፡፡

ፖሊስ ከባንክ በተገኘው ማስረጃ የምርመራ መዝገቡን በማጣራት አጠናቆ ለአቃቢ ሕግ የላከ ሲሆን አቃቢ ሕግም ከፖሊስ የቀረበውን የምርመራ መዝገብ ተመልክቶ በወንጀል ሕግ ቁጥር 359-ሀሠተኛ የብር ኖትን ማዘዋወር፣መያዝና ለፋይናስ ተቋም ማቅረብ የሚደነግገውን አንቀፅ በመጥቀስ ክስ መስርቷል፡፡

በአቃቢ ሕግ የተመሠረተውን ክስ የተመለከተው የምስራቅ ባሌ ዞን ከፍተኛ ፍርድቤት ሰሞኑን በዋለው ችሎት ተከሣሽ አብድል ሹኩር አብደላ በፋይናስ ተቋማት ላይ በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ጥፋተኛ ተብሎ በአራት አመት ከሰባት ወር እስራት እንዲቀጣ ወስኖበታል፡፡

የሙስና ወንጀል ጥቆማ ካልዎት

NCRS

ሞባይል መተግበሪያ በመጠቀም ባሉበት ሆነው ይጠቁሙ!

# መልካም ዜና

## በስህተት አካውንቱ ላይ የገባዉን ግማሽ ሚሊየን ብር የመለሰው ታማኝ ጋዜጠኛ

የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ የሆነችዉ ባለታሪካችን ሳዲያ ደጀኔ መርካቶ በሚገኝ የንግድ ሱቅ ውስጥ ተቀጣሪ ስትሆን፣ ለተለያዩ ግብይቶች ሂሳብ መክፈል ገቢንም መቆጣጠር ዋነኛ የስራ ድርሻዋ ነው።

ስራዋ ከገንዘብ ጋር በቀጥታ የተገናኘ በመሆኑ በዕለት ከዕለት የስራ እንቅስቃሴዋ ከፍተኛ ጥንቃቄ ታደርጋለች።

ይሁን እንጂ በህይወቷ ዉስጥ ይህንን ያህል መጠን ያለዉ ገንዘብ ለአደጋ ይጋለጥብኛል ብላ አስባም ተጠራጥራም አታዉቅም። የቀን ጉዳይ ሆኖ ሰሞኑን የገጠማት ክስተት በህይወቷ ዉስጥ ለከፍተኛ ጭንቀትና ዉጥረት ዳረጓት እንደነበር ተናግራለች።

ሳዲያ ደጀኔ ጥቅምት 17 ቀን 2018 ዓ.ም 495 ሺህ ብር በዲጂታል ግብይት በስህተት በሌላ ሰዉ አካዉንት ታስገባለች። ብሩ በስህተት የተላለፈዉ ደግሞ የአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ AMN ጋዜጠኛ በሆነዉ በፍቃዱ መኮንን አካዉንት ነበር።

ለጋዜጠኛ ፍቃዱ መኮንን ግማሽ ሚሊየን ብሩን በስህተት ያስገባችበትን አጋጣሚ ስታስታውሰዉ፣ ስህተቱ ከመፈጠሩ ቀደም ብሎ በሱቃቸው ላደረገው ግብይት በዲጂታል አማራጭ ክፍያ መለዋወጣቸውን ትናገራለች።

በዛው ቅፅበት ለሌላ ደንበኛ 495 ሺህ ብር ዝውውር በማድረግ የዕለት ስራዋን የቀጠለችው ሳዲያ፣ አመሻሽ ላይ በስም መመሳሰል ወደ ጋዜጠኛው ማስገባቷን ትረዳለች። በከፍተኛ ድንጋጤ ውስጥ ሆና ወዲያው ወደ ባንክ ቤት ሄዳ ጉዳዩን ለማስረዳት ብትሞክርም ሰዓቱ ምቹ አለመሆኑን ትረዳለች።

ሁኔታው እሷንና ቤተሰቧን ጨምሮ ለከፋ ጭንቀትና ሀሳብ በመዳረጉ ለሊቱን ሙሉ ያለ እንቅልፍ ማሳለፋቸውን ትናገራለች። ገንዘቡ በስህተት የተላለፈለት ጋዜጠኛ ፍቃዱም ይህንን ያህል መጠን ያለዉ ገንዘብ ከማያዉቀዉ ሰዉ ያለምንም ምክንያት በአካዉንቱ ገቢ በመደረጉ ከፍተኛ ድንጋጤ እንደተፈጠረበት ይናገራል።

ጉዳዩን ለባለቤቱ ብቻ እንዳስረዳትና " የሰዉ ሃቅ በአካዉንቴ ገቢ ተደርጓል" በሚል ጭንቀት ምሽቱን እንዳሳለፈ ያስረዳል።

ሌሊቱ እንደ አመት ነበር የረዘመባት ሳዲያ በበኩሏ በጠዋት በመነሳት አካውንቱ ወደሚገኝበት የባንክ ቅርንጫፍ ስታመራ የቀደማት አልነበረም። ለባንኩ ባለሙያዎች በስህተት ግማሽ ሚሊየን ብር ማስተላለፏን ታብራራለች። የባንክ ባለሙያዎችም ወደ ጋዜጠኛ ፍቃዱ ስልክ በመደወል የተፈጠረዉን ስህተት ያስረዱታል።

ጋዜጠኛዉ ፍቃዱም ባንኩ ስልክ ሲደዉልለትና ጉዳዩን ሲያስረዳዉ ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማዉ ተናግሯል። ዕለታዊ ስራውን አከናውኖ እንደጨረሰ ወደ አካዉንቱ የገባዉን ገንዘብ ለመመለስ ጥቅምት 18 ቀን 2018 ዓ.ም ወደ ባንኩ ሊመጣ ማቀዱን ያበስራቸዋል። ጋዜጠኛው በሰዓቱ በባንኩ በመገኘት በስም ስህተት የገባለትን ገንዘብ በታማኝነት ይመልሳል።

ምንም ወሮታ ሳይፈልግ ገንዘቡን በፍጥነት መመለሱ ከልክ በላይ ደስታን የፈጠረባት ባለታሪካችን፣ ዳግም የተወለድኩበት ቀኔ ብቻም ሳይሆን በዘመኔ እንደዚህ አይነት ታማኝ ሠው መኖሩንም እንዳምን ረድቶኛል ብላለች።

በአዲስ ሚዲያ ኔትዎርክ እየሰራ የሚገኘው ጋዜጠኛ ፍቃዱ መኮንን በበኩሉ፣ አስተዳደጌን ጨምሮ ሙያዬ የሠውን ነገር ከመፈለግ ይልቅ ታማኝ መሆንና ህዝብን ማገልገል ትልቅ ዋጋ እንዳለው አስተምሮኛል፣ለዚህም ነው ገንዘቡን የመለስኩት በማለት አብራርቷል።

ለራስም ሆነ ለሀገር ብሎም ለተሰማራንበት ሙያ ታማኝ መሆን ፍሬው ጣፋጭ ከመሆኑም በላይ በፈጣሪም ዘንድ የተወደደ መልካም ስራ በመሆኑ፣ ሁሌም ታማኝነትን የህይወታችን መርህ ልናደርግ ይገባል ብሏል።

## ታማኙ አሽከርካሪ





በደሴ ከተማ በትራንስፖርት አገልግሎት ላይ በአሽከርካሪነት የተሰማራው አቶ ተስፋዬ በላይ በተሽከርካሪው ላይ ተሳፍሮ የነበረው አቶ ምስጋናዉ አዳነ ጥሎት የወረደውን 17,000 ብር የሚገመት ሞባይል በታማኝነት ጥቅም ሳያታልለው በቅን ልቦና ሞባይሉን ለትራፊክ ፖሊስ አስረክቧል።አሽከርካሪው ስለፈፀመው መልካም አርአያነት የደሴ ከተማ አሰተዳደር ፖሊስ መምሪያ ከልብ የመነጨ ምስጋና አቅርቧል፡፡

**መልካም ሥነምግባር የህሊና እርካታ ነው!**

# ኪነ-ጥበብ

## የእጅ አመል

ቢኖረን ቢተርፈን ኪሳችን ቢሞላ፣
ብንሰጥ ብናበድር ብንተርፍ ለሌላ፣
ብንደግስ ብናቀርብ ህዝብ ብናበላ፣
ሰርቀን ባመጣነው ህዝብ ብናታልል፣
በስውር ወስደነው ጥሩ መሳይ ሆነን..
ለህዝብ ብናስመስል፤
ለጊዜው ነው እንጅ አያድግ አይቀጥል
አመል ሆኖን እንጅ...
ብዙ ነው መዘዙ ወደኋላ ሚጥል።

ጊዜው ብዙ ሆኗል ስራው ከሸመነ፣
ስሩን ከሰደደ ስሙን ካገነነ፣
ውሸት ከተካነ፣
እውነት ካመነነ፣
ቆይቷል ሙስና የእጅ አመል ከሆነ፣
ቆይቷል ሙስና የእጅ አመል ከሆነ።
ሙስና ዛሬ ላይ፣

የእጅ አመል ሆኖብን፣ የህዝቡን ላብ ንብረት፣ ምን
ብንመዘብርም፣
ሙስናን ወንጀል አካብተን ብንቃርም፣
በዘረፍነው ንብረት ቤት ሰርተን ብንኖርም፣
የህዝብን ገንዘብ ለግል ብናደርግም፣
በመጨረሻ ግን መመለሱ አይቀርም፣
ዛሬ ያለ ቢመስል ነገ አብሮን አይኖርም።